ቅጽ 3 ቁ. 2

ዴሞክራሲያ

ልዩ ስጥም፡

****
* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *
****

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ በሕብረት ግንባር ላይ ያለው አቋም

በመካሄድ ላይ ያለው ጸረ ፊውዳልና ጸረ ኢምፔሪያሊስት ትግል አብዮታዊ አቅጣጫውን ሳይለቅ ወደ ሶሺያሊዝም እንዲያመራ የግድ በአዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ጎዳና አቋርጦ ማለፍ እንዳለበት የማይታበል ሐቅ ነው፡፡ አዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮትን ለማካሄድም በላባደሩ መሪነት በአርሶአደሩ አጋርነትና በሌሎች ጭቁን መደቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች ተባባሪነት የሚቋቋም የጋራ ግንባር የፖለቲካ ሥልጣንን መጨበጥ እንደሚኖርበትም አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው፡፡ እኛም ሆነ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ አገሮች ከዚህ የተለየ ዘዴ አናገኝም፡፡ ስለዚህም አዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮትና የሕብረት ግንባር ተነጣጥለው ሊታዩ አይችሉም፡፡ ለአብዮቱ እድገት የጋራ ግንባር የግድ አስፈላጊ መሆኑ የማያወላዳ ሐቅ ነው፡፡

ኢትዮጵያን በአራቱ ማዕዘናት ያጥለቀለቀው አብዮታዊ ማዕበል በይዘቱ ጸረ ፊውዳልና ጸረ ኢምፔሪያሊስት ቢሆንም በአዲሱ ዴሞክራሲያዊ ጎዳና አቋርጦ ወደ ሶሺያሊዝም እንዳይገሰግስ ከገቱት ነገሮች መካከል ዋነኛው የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄ አለመፈታቱ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ የፖለቲካው ሥልጣን በላባደሩ መሪነት በአርሶአደሮችና በሌሎች ጸረ ፊውዳልና ጸረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ተባባሪነት በተቋቋመ የህብረት ግንባር አልተያዘም፡፡ የዚህ ተግባር አለመከናወን ከመጀመሪያውም አብዮቱን ልጓም ያስነከሰ ቢሆንም ሁኔታው ከዕለት ወደ ዕለት እየተለዋወጠ ሲሄድ ልጓሙም እየጠበቀ አብዮቱም አቅጣጫውን ይሮል ማሳቱ ይበልጥ እያገገጠ ሄዶዋል፡፡ በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካውና በሌሎችም አቅጣጫዎች ያሉትን ሁኔታዎች እንመልከት፡፡

በማናቸውም የአብዮት ወቅት የኢኮኖሚ ችግር የሚጠበቅ ቢሆንም ችግሩና መፍትሄው እየተቀራረቡ እንዲሄዱ ማድረግ ከተቀዳሚዎቹ ግዴታዎች አንዱ መሆን አለበት፡፡ በአገራችን የምንመለከተው ችግር ብዙ መንገድ ቢጓዝ መፍትሄ የተባለው አንድ ቦታ ሲዳክር ነው፡፡ የእቃዎች ዋጋ በየጊዜው እየናረ መሄድ ብቻ ሳይሆን አዝማሚያው የሚያምር አይደለም፡፡ እጅግ አስፈላጊ ተብለው የሚገመቱ ሸቀጦች ከመጠን ከመቀነስም አልፈው እልም እያሉ በመጥፋት ላይ ናቸው፡፡ የየድርጅቶቹ የምርት ውጤቶች እየቀነሱ አልፎም አልፎም ፋብሪካዎች እየተዘጉ ቢሆኑ፣ በኤርትራ ያሉት ኩባንያዎች ሥራ ማቋረጥ አንዱ ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ብዙ ችግሮችን አስከትሏል፡፡ በአንድ በኩል የሥራ አጦች ቁጥር በተፋጠነ ርምጃ እንዲያድግ ሲያደርግ በሌላው ፊት የገጠሩ አርሶአደር የኢንዱስትሪ ምርቶችን ዋጋ ለመቋቋም ሲል የሚያመርታቸው የእርሻ ውጤቶችን ገበያ እንዳያወጣ አስገድዶታል፡፡ ችግሩ በከተማውም በገጠሩም ላይ የወደቀ ቢሆንም በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ በከተማው ላይ የሚመጣው ጠኔ ቀውስ ከባድ እንደሚሆን አይጠረጠርም፡፡ ይበልጥ የሚጎዱትም ላባደሮች፣ ሥራ አጦች፣ ዝቅተኛ ንኡስ ከበርቴዎችና ሌሎች ባለዝቅተኛ ገቢዎች ይሆናሉ፡፡ የኢንዱስትሪ ውጤቶች መጠን መቀነስና ዋጋ መስቀል፣ የእህል መጥፋትና የማገዶው መወደድ በቀላሉ የሚታለፉ ችግሮች አይደሉም፣ በተለይም በላባደሩና በደጋፊዎቹ ዓይኖች ቢታዩ፡፡ ይህ ችግር ሊቃለልና ለወደፊቱም ሙሉ በሙሉ ሊፈታ የሚችለው ችግሩ የሚመለከተው ወገን ሁሉ በመፍትሄ ፍለጋው ውስጥ ሲሳተፍ ብቻ ነው፡፡ ይህም ተሳትፎ ትርጉም የሚኖረው የኢኮኖሚው ቀውስ የሚረግጣቸው ወገኖች የፖለቲካውን ሥልጣን በሕብረት ግንባር ሲጨብጡ ነው፡፡

ከኢኮኖሚው ተለይቶ የማይታየው የፖለቲካ ሁኔታም ተዘብቷል፡፡ ጸረ ፊውዳልና ጸረ ኢምፔሪያሊስቱ ትግል ከቀደመው በብዙ እጅ ልቆ ይበልጥ የህብረተሰብ ክፍሎች በውስጡ አካሎ ወደፊት እየገሰገሰ ነው፡፡ የንቃት መጠን እየመጠቀ፣ የድርጅት ገመድ እየጠበቀ ትግሉ ከእለት ወደ እለት እየከረረና እየተጠናከረ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በገጠር አርሶአደሩ በከባቢው ሥልጣን ለመጨበጥ በተደጋጋሚ ሙከራ ሲያደርግ ላባደሩ የራሱን መንግሥት ሥልጣን ካልጨበጠ ሌላ አማራጭ እንደሌለው በቅጡ እየተረዳ ነው፡፡ የላባደሩንና አርሶአደሩን አንድነት ለማፋለስ የሚረዳ እንደ ገበሬ ማኅበራት ማጠናከሪያና፣ የላባደሩን የመደብ ትግል የሚያኮላሽ የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የመሳሰሉ አዋጆች መውጣት የመንግሥቱ ፖለቲካና የጭቁን ሕዝብ ፖለቲካ ሊጣጣሙ እንዳልቻሉ ያመለክታሉ፡፡ ስለዴሞክራሲያዊ መብቶች፣ ስለጊዜያዊ መንግሥት .....ወዘተ መንግሥቱና ሠፊው ሕዝብ ያላቸው የተቃረኑ አስተያየቶችም ለሚታየው የፖለቲካ መዛባት ሌዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ቅራኔዎች ሊፈቱ የሚችሉት የጭቁን ክፍሎችን የፖለቲካ ፍላጎት የሚያሟላ ረት ግንባር ሲቋቋም ብቻ ነው፡፡ እስከዛው ቅራኔዎቹ እየከረሩ መሄዳቸው አይቀርም፣ በዚህም ት ግንባር የሚደረገው ጥሪ እየጎላና ይበልጥ አስቸኳይ እየሆነ ይሄዳል፡፡

በአ[illegible] የሚገኝ ቢሆንም መንግሥቱ በሚከተለው የ[illegible] ፖሊሲ ወደ መፍትሄው [illegible] ወደ ማባባሰ ቢያመራ [illegible]ነበር:: ይህም ለአብዮቱ ግስጋሴ [illegible] ነው:: ካለፉት [illegible] ሁለት ወሬት ወዲህ መንግሥቱና የሚ[illegible]ጠው አቅጣጫ ችግሩን ከማባባሱ አልፎ መሳውን አብዮት[illegible] አጅግ አስጊ ወደሆነ ገደል የሚመሩ ሆኖ አገኘተነዋል:: ይህም የከተት እዋች ነው:: [illegible] በለፈው የዓመከረሲያ ልዩ አትዎ የታተቀሰ ቢሆንም የአባዛው ኡስቴት በዶንሚ አንዱንመለከተው ያስገድደናል:: መንግሥቱ ለኤርትራው ችግር የመጨረሻና የማያዳግም መፍትሄ ብሎ የሚያምነው የኢትዮጵያን ሕዝብ በኤርትራ ላይ በማዝመትና የኤርትራን ሕዝብ በመጨፍጨፍ በጭር ጊዜ ጦርነቶን አሸንፍ ምዕራፉን መዝጋት ነው:: ዓላማው አራት መቶ ሺህ ያህል አርበአደሮችን ከአስራ ሶስቱ ክፍላተ ሐገራት በተለይ ግን ከትግራይ፣ ከቤገምድር፣ ከጎጃምና ከወሎ ሰብስቦ ከረምቱ ከመግባቱ በፊት በምዕራብ ኤርትራ ላይ ለማፍሰስ ነው:: በአሁኑ ወቅት አስር ሺህ ያህሉን በተለያዩ የጦር ሠፈሮች /ፍቼ፣ ደብረ ብርሀን፣ አዋሽ.....ወዘተ/በማሰልጠን ላይ ቢሆን፣ ከአሜሪካ ዘመናዊ የሆኑ ሰላሣ ኤፍ ፋይፍ ኢ ሱፐርሶኒክ ተዋጊና ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ጠይቆ ስምንቱ ያህል አገር ውስጥ ገብተው በመገጣጠም ላይ ናቸው:: አራት መቶ ኃምሳ ያህል ሐኪሞች፣ ነርሶች ከየክፍላተ ሐገራቱ ተሰብስበው ወደ ሰሜን እየተላኩ ናቸው:: ይህ ከተት በሥራ ከዋለ የሚያስከትላቸውን ሁኔታዎች ማሰቡ እንኳን አጅግ የሚዘገንን ነው:: በዚህ ዘዴ የኤርትራው ጥያቄ እንደማይፈታ፣ የመንግሥትም እቅድ በምንም ዓይነት እንደማይሳካ እሙን ቢሆንም አብዮቱን ከፍተኛ አደጋ ላይ ይጥለዋል:: በመካከላቸው መሰረታዊ ቅራኔ የሌለ ጭቁን ሕዝቦች በአሰቃቂ መንገድ እርስ በርሳቸው እንዲፋጁ ተደርጎ፣ ለአድኃሪያን ሊዘጋባቸው ቀርቶ ፈቅንም ገርበብ ብሎ የነበረው በር ተበርግዶ የመስ አገሪቱ አስናሚ ተንኮላቸው፣ የመደቡ ትግል በጭቁን ብሄሮች የርስበርስ ፍጅት ተተክቶ አብዮት ይኖራል ማለት ዘበት ይሆናል:: የጭቁን ወታደሩም ሁኔታ በዝምታ የሚታለፍ አይደለም:: ወታደራዊው መንግሥት ሥልጣን ከጨበጠበት ጊዜ ጀምሮ ከግራውም ከቀኙም ጋር ሲጠመድ የከረመ በመሆኑ ጭቁኑ ወታደር የመደብ ጠላቱን ከመደብ ወዳጁ እንዳይለይ ተደናገሯል:: ከሁሉም ጋር እየተጋጨ ሁሉም በበጉ ዓይን ለመለከተው ስለልቻለ በአገሩ በይተዋር ሊሆን በቅቷል:: በየበታውም እንደቅጠል ቢረግፍም በተለይ ከባድ እልቂት እየጋጠመው ያለው ኤርትራ ውስጥ መሆኑ የምናውቀው ሐቅ ነው:: የከተቱ አዋጅ መታወጅ ከቀደመው የባሰ ጦርነት መጧሩ ስለማይቀር ጭቁን ወታደሮች እንደቀደሞው አሁንም ለሕዝብ ባይሆን አንድን መንግሥት በሥልጣን ለማሰንበት ብቻ መርገፋቸው እየተረጋገጠ ነው:: አብዮቱን እስከሁን ከጋጠሙት አስጊ ሁኔታዎች እጅግ አለመጠን የባሰው ይህ የከተቱ አዋጅ ነው::

ቀደም ስንል የገለጽነው የሕብረት ግንባር አስፈላጊነትና ለጭቁን ያቀረብነው ያለንበት ሁኔታ ዝርዝር ጥያቄው ከመቸውም ይበልጥ በፈጣን መልስ ማግኘት እንደሚገባው ያስምኑናል:: ለአብዮቱ ከባድ ኃላፊነት አለብን:: አብዮቱን ወደፊት መራመድ የሚችል፣ ለአብዮቱ አድገት የጋት ኃይል እንኳን መንገዱ የሚከፍት ሁኔታ ከተፈጠረ ያንን ሁኔታ መርምረን መሰረታዊ እምነታችንን ሳንለቅ በዛ ሁኔታ ለመጠቀም መሞከር አብዮቱ ውስጥ የምንጫወተው ሚና የጣለብን ግዴታ ነው:: ወታደራዊው መንግሥት ሚያዝያ 12 ቀን 1968 ለአብዮታዊ ግንባር መቋቋም ያቀረበውን ጥሪ በመሰረተ አሰቡ የምንቀበለው ለዚህ ነው:: የተደረገውን የግንባር ጥሪ ከላይ እንደተሰጠ ገጸ በረከት እንመለከተውም::አብዮቱ ከተጀመረ ጊዜ ወዲህ እንደተገኙት ማናቸውም ድሎች የሕዝብ ድል አድርገን እንጂ:: ይህም የሕዝብ ትግል ውጤት ነው:: ቢሆንም የሕብረት ግንባር ሲባል፣

ሀ/ ግንባሩ በላባደሩ መደብ መሪነት፣ አርበአደሩን፣ ንኡስ ከበርቴውንና ሌሎች ጭቁን የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚያቅፍ መሆን አለበት፣

ለ/ ከላይ የተዘረዘሩት መደቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች ጸረ ፊውዳልና ጸረ ኢምፔሪያሊስት በመሆናቸው የጋራ በሆኑት ጥቅሞቻቸው አንድነት ሲፈጥሩ አብሮም የየግላቸው የሆኑ የተለያዩ የመደብ ጥቅሞች ስላሉዋቸው በየራሳቸው ትግል የሚያካሄዱ በመሆናቸው ግንባሩ የአንድነት ብቻ ሳይሆን የአንድነትና የትግል ግንባር መሆን እንደሚገባው፣

ሐ/ የተጠቀሱት መደቦችና ክፍሎች በግንባሩ ውስጥ ሊሳተፉ የሚችሉት በፓርቲ፣ በፖለቲካ ቡድን፣ በሕዝባዊ ድርጅትና እንቅስቃሴ መልክ ሲሆን ባሁኑ ወቅት ሕዝባዊ ድርጅቶች ያላቸው ፖለቲካዊ ባህርይ የላቀ በመሆኑ የሚዘነጉ አይሆኑም፣ አሁን ያሉት ጸረ ፊውዳል፣ ጸረ ኢምፔሪያሊስትና ጸረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ፓርቲዎች፣ የፖለቲካ ቡድኖች የብሄር እንቅስቃሴዎች፣ የሕዝባዊ ድርጅቶችና እንቅስቃሴዎች መገኘት እንደሚኖርባቸው፣ ስለዚህም በግንባሩ ውስጥ

1ኛ. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ
2ኛ. የብሰቡማና ሌሎች የፖለቲካ ቡድኖች፣
3ኛ. የኦሮሞ አርነት ግንባር፣ የትግራይ ሕዝባዊ አርነት ግንባር፣
የአፋር አርነት እንቅስቃሴ፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ አርነት ግንባር
.......ወዘተ
4ኛ. ከሕዝባዊ ድርጅቶችም የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማኅበር /ኢሠአማ/
የኢትዮጵያ ላባደሮች አብዮታዊ ማኅበር /ኢላአማ/፣ የገበሬ ማኅበራት፣
/ገጠርና የከተማ የሕብረት ሥራ ማኅበሮች፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር
/ኢመማ/፣ የከተማ ቀበሌ ማኅበራት፣ የኢትዮጵያ ሴቶች አስተባባሪ
ኮሚቴ /ኢሴአኮ/ የኢትዮጵያ ዘማቾች ማኅበር /ኢዘማ/.....ወዘተ